# ለምን አይገጠም? ? ?

(ከዓሊ ሁሴን)

ውድድር ተደርጎ፣
ባየር ላሩ ሩጫ፣
ተቃዋሚ በልቶ፣
ሁለት ዱካ ዋንጫ፣
ዙፋን ለወያኔ፣
ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ፣ በርጩማ!
መተንፈሻው ጠፋ፣
ተጣቦ ፓርላማ!!

ለምንስ አይገጠም? ? ?

አግዳሚ ሊሸለም፣
ለመጪው ውድድር፣
ደፋ! ቀና! ማለት፣
ካሁኑ ሲጀመር፣
ይገጠማል እንጂ፣
ቃላት ሳይመረጥ፣
ከወያኔ ጓዳ፣
ገብቶ ሲርመጠመጥ!

ለምንስ አይገጠም? ? ?

አትንኩ!? አትነካኩ!?
የአጉል አዛኝ ለቅሶ!
ሠላም ላያላብስ፣
ነፃነት ላያስገኝ፣
ወያኔን ቀልብሶ!!
ሊሰፋው ሲቃጣው፣
ድጋሚ ሊደረት፣
ይገጠማል እንጂ!
የምን ሸርተት! ሸርተት!!
ድኩም ፖለቲካ፣
አጥልቆ እንደ ጫማ፣
ዱካ ላሸነፈው፣
ሮጦ ለበርጩማ!
ይገጠም ይጣጣፍ፣
ትግሉን ላኮላሸ!
ርካሽ ህሊናውን፣
በደም ላቆሸሸ!
በደም ላበላሸ!!

ለምንስ! አይገጠም?! ?!

ለመሰረታዊ መብት
ለፍጹም ነፃነት፣
የዱክ እዬን ታሪክ
የዚህን ምሁር ውርደት፣
ተረት ተረት ብሎ
ለታዳጊ ህፃናት፣
የበርጩምዬን ጉድ ግድ ይላል ማሰተማር!
ግድ ይላል ማስጠናት!!!

ይገጠማል እንጂ!
ወጥቶ በአደባባይ!
ሃፍረት ለማያውቀው
የህዝብ ትግል ጉዳይ!!
ይጫጫር ይጣጣፍ
ሁሉም ይገጣጠም!
የትላንቱን ስህተት
ዛሬም እንዳይደግም!!

ለምንስ አይገጠም??

ክብር ስም የያዙ
ክህደት ያልነካቸው፣
የሕዝብ የሐገር ልጆች
ለጠፋው ደብዛቸው፣
እምቢኝ ለወያኔ፣
አንገዛም ብለው፣
ፍዳ ለሚበሉት
በሰንሰለት ታስረው፣
ከወዴት ደረሱ፣ የይፈቱን ጥያቄ ማንሳት ተሸማቆ!
ለመሞት የሚመኝ በፍርሃቱ ታንቆ!
በአራቱም ማዕዘን ከመሃል በሸዋ፣
አልጨበጥ ብላው ጠፍታ በርጩማዋ፣
ዱ-ካ ተረክቦ ልደታን ሊቆጥር፣
ለመጪው ሲያልም ሲጀምር ድርድር፣
ለምንስ አንገጥም?!  ለምንስ አንጥፍ?!  ለምንስ አንጭር?!
ተደፍቶ እስካደረ!  ለወያኔ ክብር ልደታን ሊቆጥር!

ለምንስ አይገጠም!